SHA Data Settlement
P.O. Box 1068
Baton Rouge, LA 70821

**የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽዎ እ.ኤ.አ እስከ ኖቬምበር 19፣ 2025 ድረስ በፖስታ ወይም በመስመር ላይ መቅረብ ይኖርበታል።**

*Lewis et al. v. Seattle Housing Authority*፣ የኬዝ ቁጥር. 24-2-16171-6 SEA

# የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ

**የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባል በመሆን የይገባኛል ጥያቄ ቅጽ ለማቅረብ ብቁ የሚሆኑት:-**

በግምት 72,000 ግለሰቦች እንደሚሆኑ ተከሳሽ በሚገምተው ቡድኑ ዝርዝር ውስጥ ይካተታሉ ተብለው የተለዩ፣ እ.ኤ.አ በኦክቶበር 2023 ወይም በዚያ አካባቢ በውሂብ ደኅንነት ላይ ባጋጠመ ክስተት ("የውሂብ ጥሰት") የግል መረጃዎ የተበረበረ እና/ወይም የተወሰደ የዩ.ኤስ ነዋሪ ከሆኑ።

የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ የሚቻልበት ቀላሉ መንገድ በበይነ መረብ አድራሻ www.SeattleHADataIncident.com፣ወይም ይህን የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ሞልተው ከላይ በተጠቀሰው መልዕክት መላኪያ አድራሻ መላክ ይችላሉ።

## በእልባት መስጫ ስምምነቱ የሚካተቱ ጥቅማጥቅሞች - ምን ሊያገኙ ይችላሉ

**ከሚከተሉት ጥቅማጥቅሞች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለማግኘት የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ:-**

**(1) ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ ለሚደርሱ ኪሣራዎች ተመላሽ ማግኘት።** ከሌላ ምንጭ ተመላሽ ካላገኙ፣ እና ኪሣራው ከውሂብ ጥሰቱ ጋር በተያያዘ የተፈጠረ መሆኑን በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል ከሆነ፣ በአንድ የቡድን አባል የወጣው ወጪ **ከ $5,000.00 ካልበጠ፣ የስምምነቱ ቡድን አባል ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ ለደረሱ በሰነድ የተደገፉ ኪሣራዎች ተመላሽ ለማግኘት ብቁ ናቸው:**

- (i) ከማጭበርበር ወይም ከማንነት ስርቆት ጋር የተያያዙ ተመላሽ ያልተደረጉ የገንዘብ ኪሣራዎች፤
- (ii) የሒሳብ ክፍያዎችን፣ የሒሳብ ባለሙያ ክፍያዎችን እና ለክሬዲት ጥገና አገልግሎት የሚከፈል ክፍያን የሚያካትት የባለሙያ ክፍያዎች፤
- (iii) እ.ኤ.አ ከኦገስት 9, 2023 በኋላ በማንኛውም የክሬዲት ሪፖርት አድራጊ ኤጀንሲ አማካኝነት በክሬዲት ላይ እገዳ ከመጣል (freezing) ወይም ከማንሳት (unfreezing) ጋር የተያያዙ ወጪዎች፤
- (iv) ከክስተቱ ዕለት ወይም ከዚያ በኋላ አንስቶ የይገባኛል ጥያቄው እስከቀረበበት ቀን ድረስ ለወጡ የክሬዲት ክትትል ወጪዎች፤ እና
- (v) እንደ ኖታሪ፣ ፋክስ፣ ፖስታ፣ ኮፒ፣ በመኪና ለተሸፈኑ የጉዞ ማይሎች እና የረጅም ርቀት የስልክ ጥሪ ክፍያዎች ያሉ የተለያዩ ወጪዎች።

የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት የክፍያ ተመላሽ ጥያቄዎቻቸውን የሚደግፍ ተገቢ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው። ይህም ደረሰኞችን ወይም ሌሎች የወጡ ወጪዎችን መዝግበው የያዙ በይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው "በራሱ ያልተዘጋጁ" ሰነዶችን ሊያካትት ይችላል። እንደ በእጅ የተፃፉ ደረሰኞች ያሉ "በራስ የተዘጋጁ" ሰነዶች፣ በራሳቸው፣ ተመላሽ ገንዘብን ለመቀበል ሊቀርቡ የሚችሉ በቂ ማስረጃዎች አይደሉም፣ ነገርግን ሌሎች የቀረቡ ሰነዶችን ግልፅነት ለመጨመር ወይም ለመደገፍ እንደቀረቡ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

**(2) በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ ማካካሻ።** የእልባት መስጫ ስምምነቱ ቡድን አባላት እስከ አራት(4) ሰዓታት ድረስ፣ በሰዓት $25፣ ከፍተኛው እስከ $100 ድረስ፣ በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ የካሳ ይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ብቁ ናቸው። ለውሂብ ጥሰቱ ምላሽ ለመስጠት የተወሰዱ እርምጃዎችን እና እያንዳንዱ እርምጃ የወሰደውን ጊዜ የሚያሳይ አጭር መግለጫ ("ይፋዊ ማረጋገጫ") ያስፈልጋል።

**(3) አማራጭ የገንዘብ ክፍያ።** ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ በሚደርሱ ኪሣራዎች እና በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ በሚከፈሉ የገንዘብ ማካካሻዎች ምትክ፣ የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ አባላት ከፍተኛው እስከ $100 የሚደርስ የገንዘብ ክፍያ ይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ መምረጥ ይችላሉ። ይህንን የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ሰነድ ማቅረብ አያስፈልግም። የሚሰጠው የገንዘብ ማካካሻ መጠን የሚጨምረው ወይም የሚቀነስ ለእያንዳንዱ ሰው ድርሻ ተመጣጣኝ የሆነ ልክን መሰረት በማድረግ በቀረቡት ትክክለኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ብዛት እና ለእነዚህ ክፍያዎች በተያዘ በጀት መጠን ላይ በመመርኮዝ ነው።

**የይገባኛል ጥያቄዎች እ.ኤ.አ እስከ ኖቬምበር 19 ቀን 2025 ድረስ በመስመር ላይ በመቅረብ ወይም በፖስታ ሳጥን ቁጥር መላክ አለባቸው።**
**የይገባኛል ጥያቄ ቅፅዎን በፖስታ ለመላክ በዚህ ቅፅ አናት ላይ ያለውን አድራሻ ይጠቀሙ።**

## የእርስዎ መረጃ

ስምዎን እና የመገኛ አድራሻዎን ከዚህ በታች ይስጡ። ይህንን የይገባኛል ጥያቄ ቅጽ ከላኩ በኋላ የመገኛ አድራሻዎ መረጃ ከተቀየረ ለይገባኛል ጥያቄ ጉዳይ አስተዳዳሪው ማሳወቅ አለብዎት።

**ስም ከነአባት** | **የአያት ስም**

**የጎዳና (Street) አድራሻ**

**ከተማ** | **ስቴት** | **ዚፕ ኮድ**

**የኢሜይል አድራሻ** | **የስልክ ቁጥር** | **የይገባኛል ጥያቄ መለያ ቁጥር፣ የሚታወቅ ከሆነ**

## ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሣቢያ ለሚደርሱ ኪሣራዎች ተመላሽ ክፍያ

☐ በጠቅላላው እስከ $5,000.00 የሚደርስ ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሣቢያ ለሚደርስ ኪሣራ ካሳ**ተመላሽ ለማግኘት ጥያቄ እያቀረቡ ከሆነ** በዚህ ሳጥ ውስጥ ምልክት ያድርጉ
**ትክክለኛ፣ ተመላሽ ያልተደረገ የገንዘብ ኪሣራን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ይኖርብዎታል።**

*እርስዎ የሚያቀርቡትን የድጋፍ ሰጪ ሰነድ በመግለፅ ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይሙሉ።*

| የቀረበው ሰነድ መግለጫ | መጠን | ቀን |
|---|---|---|
| ምሳሌ:- የክሬዲት ጥገና አገልግሎቶች ደረሰኝ | *$100* | ወር/ቀን/ዓመት |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| **ይገባኛል ጥያቄ የቀረበበት ጠቅላላ መጠን:-** | | |

☐ ከላይ የዘረዘሩትን ከኪስ ውጪ የተደረጉ ወጪዎች እና ክፍያዎች በትክክል የተከሰቱ እና በውሂብ ጥሰቱ ምክንያት የተፈጠሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ሣጥን ውስጥ ምልክት ማድረግ አለብዎት።

## ለባከነ ጊዜ ማካካሻ (“በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል የባከነ ጊዜ”)

ብቁ የሆኑ ግለሰቦች እስከ አራት(4) ሰዓታት ለሚደርስ የባከነ ጊዜ በሰዓት $25፣ ከፍተኛው እስከ $100 ድረስ ለሚደርስ ተመላሽ ይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ብቁ ለመሆን፣ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች የባከነውን ጊዜ ምንነት የሚገልጽ አጭር ማረጋገጫ ማቅረብ እና በውሂብ ደኅንነት ላይ ባጋጠመው ክስተት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ለዚህ ጥቅማጥቅም ከሚቀርበው ማረጋገጫ በላይ ምንም ተጨማሪ ሰነድ አያስፈልግም።

ይገባኛል ጥያቄ የቀረበበት ሰዓት (እስከ 4) [ ] 1 ሰዓት ($25) [ ] 2 ሰዓት ($50) [ ] 3 ሰዓት ($75) [ ] 4 ሰዓት ($100)

ማረጋገጫ:- ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

## አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ

☐ አማራጭ የካሳ ጥሬ ገንዘብ ክፍያ ለመቀበል ከፈለጉ በዚህ ሣጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉ።

ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በወረቀት ቼክ ሊከናወን ይችላል። አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ለእልባት ስምምነቱ ክፍያ የተያዘው የፈንድ/በጀት መጠንን የሚያሟጥጡ ከሆነ አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ መጠኑም *በተመጣጣኝ መልኩ* ሊቀንስ ይችላል (ሁሉም ከኪስ ወጪ በተደረጉ ገንዘቦች ሳቢያ የተፈጠሩ ኪሳራዎች፣ ሊረጋገጡ ለሚችሉ የባከኑ ጊዜዎች፣ የእልባት ስምምነቱ ጉዳይ አስተዳደር ወጪዎች፣ የአገልግሎት ክፍያዎች፣ እና የከሳሽ ጠበቃዎች ክፍያ እና ወጪዎች ከተከፈሉ በኋላ)።

## የክፍያ ምርጫ

እባክዎን ከሚከተሉት የክፍያ አማራጮች ውስጥ **<u>አንዱን</u>** ይምረጡ:-

☐ **PayPa** - የ PayPa ኢሜይል አድራሻዎን ያስገቡ: ______________________________

☐ **Venmo -** ከ Venmo መለያዎ ጋር የተገናኘውን የሞባይል ቁጥር ያስገቡ: __ __ __-__ __ __-__ __ __ __

☐ **Zelle -** ከ Zelle መለያዎ ጋር የተገናኘውን የሞባይል ቁጥር ወይም የኢሜል አድራሻ ያስገቡ:

የሞባይል ቁጥር: __ __ __-__ __ __-__ __ __ __ ወይም የኢሜይል አድራሻ: ______________________________

☐ **በቼክ -** ክፍያው በዚህ ቅጽ ላይ በተጠቀሰው አድራሻ በፖስታ ይላካል።

## ማረጋገጫ እና ፊርማ

በዚህ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የቀረበው መረጃና ማንኛውም ድጋፍ ሰጪ ሰነድ እስከማውቀው ድረስ እውነተኛ እና ትክክለኛ እንደሆነ እና የሐሰት ምስክርነት ብሰጥ ቅጣት እንደሚከተለኝ በመረዳት ቃሌን እሰጣለሁ እንዲሁም አረጋግጣለሁ። ያቀረብኩት ይገባኛል ጥያቄ ለማረጋገጫ ምርመራ የሚቀርብ መሆኑን እና ያቀረብኩት የይገባኛል ጥያቄ የተሟላ እና ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት ተጨማሪ መረጃ እንድሰጥ በእልባት ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው ሊጠየቅ እንደሚችል እገነዘባለሁ።

______________________ ______________________ ______________________

ፊርማ ስም ቀን